EMBASSY OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
BRUSSELS, BELGIUM

## 1. አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን ጥቅምት 9 ቀን 2017 ዓ. ም. በቤኔሉክስ አገሮች ከሚገኙ የዳያስፖራ አባላት ጋር ባደረጉት የትውውቅ መድረክ ካስተላለፉት መልእክት የተወሰደ፣

- ***ከቡራትና ከቡራን ጥሪ የተደረገላችሁ በቤኔሉክስ አገራት የምትገኙ ኢትዮጵያዊያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች/ Friends of Ethiopia፣***
- ***ከቡራን ምክትል የሚሲዮኑ መሪዎች፣ ዲፕሎማቶች እና ሠራተኞች፣***

ከሁሉ አስቀድሜ በዛሬው የትውውቅ መርሃ-ግብር ላይ ለመገኘት ጥሪያችንን አክብራችሁ የጋራ ቤታችን ወደ ሆነው የኢትዮጵያ ኤምባሲ እንኳን በደህና መጣችሁ ለማለት እወዳለሁ። ***ለእንግዶቻችን በእራሴ እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት ስም ምስጋናዬን ከፍ ባለ አክብሮት እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ።*** በዚህ አይነት የተረጋጋ መንፈስ እንድንገናኝና እንድንተዋወቅ፣ ***በተለይ እናንተን ጊዜአችሁን ሰውታችሁ የመጣችሁት!*** በበጎ አገልግሎት መንፈስ ስለተገናኘን ይህን ላዘጋጀ አምላክ ክብርና ምስጋና ይሁን።

የዚህ መርሃ-ግብር ዋና ዓላማ ***በጋራ የሀገራችን ኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና ክብር ለማስጠበቅ እኔና እዚህ ኤምባሲ ውስጥ ያለነው ሰራተኞች በቂ ስላልሆን የሁላችሁንም ድጋፍ የምናገኝበትን መደላድል መፍጠር ነው።*** አብረን ለመስራት የመጀመሪያው እርምጃ መተዋወቅ እንደመሆኑ፣ እዚህ ቤልጅየም ስራ መጀመሬን፣ ኔዘርላንድስና ሉግዘምበርግ ደግሞ ከአመቱ መጨረሻ በፊት ለመጀመር እንሰራለን፡፡ ወገኖቼ እኔና ባልደረቦቼ ማንኛውንም ስርዓት የተከተለ የሙብትና የጥቅም ጥያቄ የሚመለከት አገልግሎት ለመስጠት፣ ለማስተናገድና ቅሬታዎችን ተቀብለን እዚህ በራሳችን እንዲሁም አገር ቤት በዋናው መስሪያ ቤት አማካኝነት መፍትሄ እንዲሰጥ ለማድረግ ሙሉ ፍላጎት አለን፡፡ በዚህ ረገድ ዝግጁ መሆናችንንም ዛሬ ላልተገኙት ወገኖቻችን በሙሉ እምነት አሳውቁልን።

***መንግሥትና ህዝብ የሰጠንን አደራ ለመፈፀም ስንሰማራ የሚከተሉትን ማስተዋል ጠቃሚ ነው፡፡***

1. ስራችን የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚመለከቱ የፖለቲካና ሰኪዩሪቲ ወይም ጂኦ-ፖለቲካዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የፐብሊክ ዲፕሎማሲና የዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ሰፋፊ ተግባራትን ያካትታል። የእነዚህ ስራዎች አድማስ ብሄራዊ፣ ክልላዊና ዓለም አቀፋዊ ይዘት አለው። ስለዚህ በጋራ ጉዳይ ለመነጋጋር ወይንም ድጋፋችሁን ፈልገን ጥሪ ስናስተላልፍላችሁ ጊዜና ቦታ ሳይወስነን፣ ***ኢትዮጵያን ከፊት በማድረግ ልንረዳዳ ይገባል። የሌሎች አገራት ተወላጆችን መልካም ተሞክሮ እያየን በተሻለ አብረን ለመስራት የሚሳነን ስላልሆንን ሌላው ዓለምና ዜጎች እንዲያከብሩን ከፍ ብለን እንገኝ።***

2. ሁሉም ሰው ለግል አስተሳሰቡና ዓላማው የሚመቸውን የማድረግ በተፈጥሮ የተሰጠ ጸጋውን ማንም አይጋፋም፡፡ ዳሩ ግን እርሱንም ቢሆን በአግባቡ ለመጠቀምና ሃሳብን በንግግርና በምክክር ወደ ተግባር ለማሸጋጋር ***በሚያሰባስበን ጥላ ስር እዚህ በኤምባሲያችን*** እየተገናኘን መነጋገር ተገቢ ነው፣ ያለንን እድል በአግባቡ እንጠቀምበት። ማንኛውንም ሃሳብ በሰላማዊ መንገድ ማንጸባረቅ፣ ***እርስ በእርስ በመከባበር ከአባቶቻችን በተወረሰ የባህልና ትውፊት ሃብታችን መሠረት እንሰራለን የሚል ጠንካራ እምነት አለን።***

3. የኢትዮጵያን አንድነት ለመገንባት ያለብንን ተግዳሮት በመገንዘብ ***በመንግስት ተቋማትና በሕዝባችን*** የሚከናወኑ፣ በተለይም ***ሰላምን የማጽናት እና የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ጥረቶች፣*** በሃገረ-መንግሥት ግንባታ ሂደት የጋራ መግባባትን ለማረጋገጥ ልናሳድገው ስለሚገባ የመወያየት የዲሞክራሲ ባህል፣ ይልቁንም ደግሞ ***የምትኖሩባቸውን አገሮች ተሞክሮ በማገናዘብ ጭምር ሁልጊዜ ለመነጋገር መዘጋጀት ጠቃሚ ይሆናል።***

4. እንደምታውቁት ***ኢትዮጵያ በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ምዕራፍ ሁለት*** (***Home Grown Economic Reform I 2019 to 2022 and Home Grown Economic Reform II focusing on the Macroeconomic Reform 2024 to 2026)*** በመሰረተ-ልማት ግንባታ፣ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በማዕድን፣ በዲጂታላይዜሽን እና በቱሪዝም መስኮች የተቀናጀ የልማት እቅድ ይዛ እየሰራች ነው። ***የኢትዮጵያ Flag-Ship Project የሆነው የህዳሴ ግድብም ወደ መጠናቀቅ ተቃርቧል፣ የጊቤ ሶስት፣ የገናሌ ዳዋ እና ሌሎችም የረጅም ዓመታት እንደምታ ያላቸው ፕሮጀክቶች ግንባታም እየተፋጠነ ይገኛል።*** በቅርቡ የተጀመረው የኢትዮጵያን ከተሞች ከዘመኑ ጋር የሚጓዙ የማድረግ ሥራ ጥሩ ውጤት አሳይቷል። ይህ ስራ ከተሞቻችን ከሚታይባቸው መሠረቱ የተበላሸ አሰፋፈር የመላቀቅ ጅምር ስለሆነ፣ የዜጎችን ዘላቂ ጥቅምና ምቾት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲቀጥል ማበረታታት እና ለመጪው ትውልድ መልካም መነሻ እንዲሆን ልንሰራ ይገባል።

5. እስካሁን ያሳካናቸው አገራዊ ክብርን የማረጋገጥ፣ ሰላም የማስፈን እና ልማትን በየዘርፉ የማስፋፋት ስራዎች የማይታበሉ ናቸው። የሚታዩና የሚዳሰሱ ስለሆኑ የትም አይሄዱብንም፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ***አንዳቸውም ያለ ተግዳሮትና ፈተና እንዳልተካናወኑ መረዳት ይገባል።*** ስለዚህ የሚጠበቅብን ከባድ ስራ ጅምሩን ማስፋፋት፣ ማዘመን እና ማበልጸግ ነው። ተግዳሮቶቻችንን አስከፊ የሚያደርጋቸው በውጭ በሚሰነዘር ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነትና የፖለቲካ ተጽዕኖ እንዲሁም የውስጥ ክፍተቶቻችንን በማጥናት ሃብት በማፍሰስ ጭምር የማባባስ ሴራ የሚፈፀምብን መሆኑ ነው። አገራችን በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ለእነዚህ ፈተናዎች ተጋላጭ ሆና መቀጠሏ የማይቀርልን ስለሆነ፣ ***በተግባርና በመንፈስ ብሄራዊ ህልውናችንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ የጋራ ግንዛቤ ይዘን ልንደጋገፍ ይገባል፡፡***

ከዚህ አንፃር ማንኛውንም አጀንዳ በሰከነ መንፈስ፣ በንግግርና በድርድር ብቻ የመፍታት ባህልን ለማዳበር መስራት ስላለብን፣ ይህም ***21ኛውን ክፍለ-ዘመን የሚመጥን በመሆኑ አገራዊ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ስርዓት እንዴት እንገንባ የሚል የጋራ Equation በማስቀመጥ ለመፈፀም መረባበብ ይጠይቃል፡፡*** ብዙ አማራጭ ሃሳቦችን እያነሳን መወያየት፣ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድና ማድመጥ፣ መረዳዳትና ለአገራችንና ለህዝባችን የሚጠቅመውን ሁሉ እየቀመርን ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ተገቢ ይሆናል፡፡ ***እዚህ ኤምባሲ ያለነው አገልጋዮች ልባችንም ቢሮአችንም ክፍት ነው።*** ከፍ ብሎ ለማሳየት እንደተሞከረው፣ ***በአገልግሎቶችም ሆነ በሰፋፊ ሃሰቦች ውጤት ለማስመዝገብ የሁላችሁም ትብብር እንዳይለየን በማክበር እንጠይቃለን።***

ሃገራችን ኢትዮጵያ በአለም መድረኮች የምትወከልባቸው ኤምባሲዎች ወይንም ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ጥቂት በመሆናቸው፣ በየአገሩ የሚገኙ ለወገን ጥብቅና የሚቆሙ የዳያስፖራ አባላት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ካደረጉ መልካም ክንውን ይኖረናል፡፡ ***ኢትዮጵያውያን በአካል የትም ብንኖር በሃሳብ ግን ከእናት ሀገራችን መለየት አይሆንልንም።*** ይህ መልካም እሴት የሚሲዮኑ ዲፕሎማቶች በተወከሉበት ሀገር ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም በወገኖቻቸው እየተደገፉ ውጤታማ ስራ እንዲያከናውኑ መልካም መሰረት ሆኖ ያገለግላል። ***በዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ትብብር የዳያስፖራ ኮሚኒቲ አባላት ሚና ወሳኝ ሚና አላቸው። እስካሁን ለእናት ሀገር ጥብቅና በመቆም የተለያዩ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ ብሔራዊ ጥቅምና ክብር ላይ የተቃጡ አጥፊ ድርጊቶችንና ፍላጎቶችን በጋራ አምክነናል። በአንድነት በመቆም በአለም አደባባይ የተቃውሞ ድምፅ በማሰማት አገራችንን ታድገናል፣ ይሄ ወደፊትም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።***

በአፍሪካ ቀንድ ያለው የጂኦ-ፖለቲካዊ ትግል እና የተፅእኖ ማሳደሪያ ቅርምት እንዲሁም የአፍሪካ Axis and Alliance ፈጠራን በመረዳት አገርና ህዝብን ተቀባይነት ከሌለው ጫና ወይም ጣልቃ-ገብነት በመከላከል ረገድ ያከናወንነውን አኩሪ ታሪክ መነሻ በማድረግ፣ ለወደፊት ለሚጠበቀው የማይቀር ተግዳሮትም የሚመጥን ምላሽ ለመስጠት ቦታና ጊዜ ሳይገድበን ***ትልቋን ኢትዮጵያ በልባችን አኑረን እንታገል።*** ጎን ለጎንም ወገናችንን ከረሃብ ውርደት፣ ከጨለማ እና ከኋላ-ቀርነት ለማላቀቅ የተጀመሩ ጥረቶችን በመቀጠል፣ ግንባታው በመጠናቀቅ ላይ የሚገኘውና ከፍ ያለ ወጪ ለሚጠይቀን ***ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ግዢና ስጦታ በማሰባሰብ፣ በገበታ ለሀገርና ገበታ ለትውልድ ለመሳሰሉ ፕሮጀክቶች የተደረገውን ርብርብ በማስቀጠል የአገር ግንባታውን እናግዝ። በአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት ምዕራፍ አንድ የንፅሕና ቦታዎች ግንባታ የተደረገውን ዓይነት ፈጣን፣ ውጤታማና impactful ስራ በማከናወን እራሳችንን የሚያረካ ስራ ሁሌም በአእምሯችን አኑረን እንድንሰራ ጥሪ እንናስተላልፋለን።*** እስካሁን ላጋጠሙ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ለተጎጂዎች ላበረከታችሁት ድጋፍና የልማት ተሳትፏችሁ ህዝባችን ባለውለታ ነው። ይህ ከሀገር ወዳድነትና ከሰብአዊነት የሚመነጭ መልካምነት ለወደፊትም መቀጠል አለበት፡፡

***ከአገራችሁ ጋር ያላችሁን ትስስር በማጠናከር፣ የአብሮነት ባህልን በማዳበር፣ ለአገራችን ብሔራዊ ክብር እና ጥቅም ጥብቅና በመቆም፣ በአገራችን የሚታዩ ግጭት ቀስቃሽ አስተሳሰቦች እንዲወገዱ በሃሳብም በጸሎትም በማገዝ፣ ልዩነቶችን በሰከነ መንገድ በውይይት ለመፍታት***

***በመንግሥት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን በማበረታት መረዳዳት አለብን።*** በየግላችሁ ወይም በመደራጀት በልማት ሥራዎች ለመሳተፍ እና ተጠቃሚ ለመሆን አተኩረን በጋራ መስራት አለብን። ኢትዮጵያ ለእራሷ ብቻ ሳይሆን በፓን-አፍሪካኒዝም መርህ ለመላው ጥቁር ህዝብ ዓርማ ስለሆነች ሚሲዮኑና እናንተ በዚያ ከፍታ ልክ ልንሰራ ይገባል። ተሳትፎአችሁ በሁሉም መስክ ይጠናከር።

***አምላክ ይርዳን! አገራችንን ይጠብቅልን! አሜን።***

## II. <u>በዳያስፖራ አባላት የተነሱ ሃሳቦች</u>

ከተሰብሳቢ የዳያስፖራ አባላት ኢትዮጵያውያን የዳበረ ባህል እና አገር-በቀል ግጭት የመፍታት ተሞክሮ እያለን የምንገዳደለው ለምንድን ነው? ይህ ጥያቄ በሁላችንም አእምሮ ሊነሳና መልስ ሊያገኝ ይገባል የሚል ዐብይ አስተያየት ተሰንዝሯል። በሌላ በኩል ሁላችንም ለአገራችን ባለዕዳ በመሆናችን የየበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት ሰብዓዊና ሞራላዊ ግዴታ እንደአለብን፣ አገር ውስጥ ብዙ መልካም ጅምሮች አሉ እነርሱም እያደጉ እንዲሄዱ እንቅፋት የሚፈጥሩትን በእውቀት እና አመክንዮ ማሸነፍ እንደሚገባ፣ ኢትዮጵያውያን አሁን ያሉብንን እርስ በእርስ የመጠላላት እና የመከፋፈል አባዜ አስወግደን የጠላትን ሴራ በተገነዘበ አኳኋን ልንቆም እንደሚገባ ተገልጿል።

የአገራችንን ሰላምና ደህንነት ስለማፅናት፣ ስለ ባህር ተደራሽነትና ዓለም አቀፋዊ አንደምታው፣ ችግሮችን በድርድር ስለመፍታት፣ ስለ ሕገ-መንግሥት ማሻሻል፣ ስለመልካም አስተዳደር መጓደል(ሙስና) ለዳያስፖራው ምቹ የኢንቨስትመንት እና ቢዝነስ እድሎች ስለሚመቻችበት ሁኔታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

በሌላም በኩል የኢሚግሬሽና ዜግነት አገልግሎት የOnline Visa አሰራር እየፈጠረ ስላለው ችግር፣ የተገልጋዮችን ችግር ለመፍታት የዝግጁነት መጓደል ስለመኖሩ፣ በፓስፖርት እና በትውልደ-ኢትዮጵያውያን መታወቂያ እድሳት የአገልግሎት ተግዳሮቶች ጥያቄዎችና ቅሬተዎች ቀርበዋል።

ለተነሱት ጥያቄዎች መልስ የሚሆነው የአመለካከት፣ የፖለቲካና የድርድር ባህልን በማዘመን፣ የተቋማትን ግንባታ በማጠናከር፣ ዘመናዊ የመረጃ ፍሰትና ማኔጅመንትን ማሻሻል እንደሆነ በመጠቆም ዝርዝር ማብራሪያ ተሰጥቷል። እንደዚያም ሆኖ የተነሱት ነጥቦች በአንድ ቀን ውይይት የተሟላ መልስ ሊያገኙ ስለማይችሉ ተጨማሪ ጥያቄና ሃሳቦችንም እያነሳን ለመነጋገር የመነሻ ጽሁፎች እየተዘጋጁና ማስረጃዎች እየቀረቡ ጭምር ለመወያየት ስምምነት ላይ ተደርሷል።